# በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን በየሳምንቱ ቅዳሜና እሁድከ 4- 6 ሰዓት ለሚካሄደው መርሐ ግብር በምድብ አምስት (ከ10ኛ - 12ኛ ክፍል) ለሚገኙ ተማሪዎች የተዘጋጀ ዓመታዊ ትምህርት

## ምድብ 5 (ከ10ኛ - 12ኛ ክፍል)

## 22 ኛ ሳምንት

## ዓለም ሁሉ የተቃወመው ቅዱስ አትናቴዎስ

**ዓላማ**
- እስከሞት ድረስ በእምነታችን መጽናት እንደሚኖርብን መማር፡፡

**ጥቅስ**
- ዕብ 13*7

**ምንባብ**
- ዕብ 13*1- ፍጻሜ፡፡
- ሃይማኖተ አበው ዘቅዱስ አትናቴዎስ፡፡

**መግቢያ**
- ያለፈውን ሳምንት ትህምርትና ጥቅስ መከለስ፡፡
- በእጃችሁ የተሰጣችሁ ሥዕል ላይ የምታዩት ቅዱስ ማነው?

**የትምህርቱ ዝርዝር መግለጫ**
- አትናቴዎስ በ296 ዓ.ም በእስክንድርያ ተወለደ፡፡ ወላጆቹ ክርስቲያን መኾን አለመኾናቸው አልታወቀም፡፡
- ቅዱስ አተናቴዎስ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ጠበቃ ነበር፡፡
- አትናቴዎስ ከከሃድያን ጋር በመከራከር የክርስቲያን ሃይማኖትን ትክክለኛ ትምህርት ለዓለም ያስተዋወቀ አባት ነበር፡፡ አባቱ ባለጠጋ ቢሆንም በሕፃንነቱ ሞቶበት ነበር፡፡
- እናቱ ግን ተንከባክባ አሳደገችው ፡፡ ከክርስቲያኖችም ትምህርት ቤት አስገብታ እንዲማር አደረገችው፡፡
- አትናቴዎስ ከክርስቲያን ልጆች ጋር እየዋለ ሲጫወቱ ፡ ሲናገሩ ፡ ሲጸልዩና ፡ እርስ በርሳቸው የነበራቸውን ፍቅር ሁለ ይመለከት ነበር፡፡
- ልጆቹም ሃይማኖትህ ምንድን ነው ? ብለው ጠየቁት፡፡ እርሱም የማመልከው ጣዖት ነው አላቸው ፡፡ ልጆቹም ጣዖት እኮ አምላክ አይደለም ፡ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው አሉት ፡፡ አትናቴዎስም ክርስቲያን መሆን እፈልጋለሁ አላቸው ፡፡

  **ጥየቄ**
  1. በሥዕሉ ላይ የምትመለከቱት ቅዱስ ማነው ?
  2. የቤተሰቦቹ ሃማኖት ምንድን ነበር ? ከወላጆቹ አስቀድሞ የሞተው ማነው ?
  3. አትናቴዎስ የተማረው በምን ዓይነት ትምህርት ቤት ነበር ?
  4. ጓደኞቹ ክርስቲያኖች ልጆች ምን አሉት ?
- አትናቴዎስም መጠመቅ ፈለገ እናቱ ግን ከለከለችው፡፡ ክርስትያኖችን የሚጠላ ጠንቋይም አምጥታ እንዲመክረው አደረገች፡፡ በመጨረሻ ግን ወደ እስክንድርያ ሄደው እርሱና እናቱ ተጠመቁ፡፡ እናቱም ወዲያው አረፈች፡፡ አትናቴዎስም በእስክንድርያ በነበረው ፓትርያርክ ዘንድም ተቀመጠ፡፡
- ከዕለታት አንድ ቀን ከትምህርት ቤት ጓደኞቹ ጋር ኹኖ እሱ እንደ አጥማቂ ቄስ ጓደኞቹ እንደ ተጠማቂ ኹነው ሲጫወቱ በጊዜው የነበረው የእስክንድርያ ፓትርያርክ እለእስክንድሮስ/አሌክሳንድሮ/ በመንበረ ፓትርያርኩ ሰገነት ላይ ኹኖ ይመለከት ነበር፤ ነገሩ ገርሞት መልእክተኛ ልኮ ሕጻናቱን አስጠርቶ ቢጠይቃቸው የጥምቀት ምሥጢር እየሰራን ነው የሚያጠምቀንም ይኸ ልጅ ነው ብለው ወደ አትናቴዎስ አመለከቱ ፡፡
- ፓትርያርኩም በአትናቴዎስ ሕይወት እጅግ ተደሰተ፡፡
- በኋላም ልብሰ ምንኩስና አልብሶ ለመንበረ ፓትርያርኩ ሊቀ ዲያቆን አድርጎ ሾመው፡፡ ሊቀ ዲያቆንነት በዚያን ጊዜው ሥርዓት የፓትርያርኩ ረዳትና ሥራ መሪ ማለት ነው፡፡ በ325 ዓ.ም በተደረገው የኒቂያ ጉባኤ አትናቴዎስ ፓትርያርኩን እለእስክንድሮስን ተከትሎ ተሳትፏል፡ በጉባኤውም ላይ ለኦርቶዶክሳዊት እምነት የሚረዱ ጥቅሶችን እያጠናቀረ ያቀርብ የነበረ እሱ ነው፡፡ ከጉባኤው ፍጻሜ በኋላ ፓትርያርኩ እለእስክንድሮስ ሲያርፍ አትናቴዎስ ተመርጦ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ኾነ፡፡
- አትናቴዎስ በቤተክርስቲያንም በቅንነት ያገለገል ነበር፡፡ መጻሕፍትን በማንበብ ጸሎትንም አብዝቶ በመጸለይ በቅንና ንጹሕ ሕይወት ይኖርም ነበር፡፡
- አትናቴዎስን በመናፍቃን ከሳሽነት ሥጋውያን ነገሥታት ሲያሳድዱት ኑረዋል፡፡ ብዙ ጊዜ ከመንበሩ እየለቀቀ ተሰዷል፡፡ የአርዮስ ክህደት በኒቅያ ከተወገዘ በኋላ ለ50 ዓመታት ያህል አትናቴዎስንና የቤተ ክርስቲያን
- አባቶችን ሲያስቸግር ኑሯል፡፡ አትናቴዎስ ግን ለመከራ የማይንበረከክ ቆራጥ አባት ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን አትናቴዎስን ለማስፈራራት «አትናቴዎስ ዓለም ኹሉ ይቃወምሃል ምን ይሻልሃል» ቢሉት አትናቴዎስ
  ባጭሩ መልሰ «እኔም እቃወመዋለሁ» ብሎ መለሰ ይባላል፡፡ ስለዚህም አትናቴዎስ «አትናቴዎስ ፀረ ዓለም» የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር፡፡ ዘወትር ማንንም ሳይፈራ እውነትን ይመሰክር ነበር ፡፡
- አትናቴዎስ ለእግዚአብሔር፡ ለምዕመናንና፡ ለእውነት ከነበረው ጽኑ ፍቅር የተነሣ አምስት ጊዜ ታስሯል፡፡ እግዚአብሔር ግን ከእርሱ ጋር ሆኖ ኃይልን ድልን ይሰጠው ነበር፡፡

  **ጥያቄ**
  1. ለእውነት የቆመው ፓትርያርክ ስም ማን ነበር ?
  2. የአትናቴዎስ የክብር ስም ማነው ? ለምን ይህ ስም ተሰጠው ?
- **መምህር** ፡ ለልጆቹ ቅዱስ አትናቴዎስ ለአርዮስ ክህደት የሰጠውን ምላሽ አስመልክቶ ማብራርያ መስጠት ይችላሉ፡፡ ጸሎተ ሃይማኖትንም ያስጠኗቸውና እንዲጸልዩ ያድርጓቸው ፡፡
- አትናቴዎስ ሃይማኖቱን ጠብቆ ሩጫውን የፈጸመው በ375 /364/ ዓ.ም ነው፡፡ ዕረፍቱም ግንቦት 7 ቀን ነው፡፡
- ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትን ለማስተማር ከምትጠቀምባቸው የሊቃውንት መጻሕፍት ብዙዎቹ የተጻፉት በዚህ ፓትርያርክ ብዕር ነው፡፡ አትናቴዎስ «አትናቴዎስ ሐዋርያዊ፣ አትናቴዎስ ትልቁ» ይባላል፡፡ ለእኛም የመጀመሪያውን ጳጳሳችንን ፍሬምናጦስን ቀብቶ የሾመልን ይኸው ፓትርያርክ ስለኾነ በተለይ እናስታውሰዋለን፡፡ ለእስክንድርያ መንበር ከቅዱስ ማርቆስ ቀጥሎ ሃያኛ ፓትርያርክ ነው፡፡

**ማጠቃለያ**
- አትናቴዎስ ወጣት ቢሆንም በሃይማኖቱ ግን ጠንካራ ነበር ፡፡
- አትናቴዎስ ለእግዚአብሔር ቃል ጥሩ ግንዛቤ ነበረው፡፡ ከዚህም የተነሣ ለእምነቱ መከራከርና መርታት ችሎ ነበር ፡፡

**ተግባር**
- ✓ ወይም X ምልክት በማድረግ ትክክል የሆነውን ወይም የልሆነውን ዐረፍተ ነገር ያሳዩ፡፡
  - የአተናቴዎስ ወላጆች ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡
  - ከክፉ ሰዎች ጋር ተቀላቅለን ስንኖር እግዚአብሔር በእኛ ደስ ይለዋል፡፡
  - አተናቴዎስ የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ጠበቃ ተብሎ ይጠራ ነበር፡፡

**ይቆየን፡፡**

አዘጋጅ፡ ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ - የካቲት ፳፩ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.